# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
# ሰበር ሰሚ ችሎት

የመ/ቁ. 15493

ዳኞች: - አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍስሐ ወርቅነህ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
ወ/ሮ ስንዱ አለሙ
ወ/ሪት ሂሩት መለሰ

አመልካች: - አቶ ጳውሎስ ሩምቾ
መልስ ሰጭ: - ወ/ሮ ጫልቱ መርዳሳ

ውል የግዴታዎች መቅረት - ስለ ይርጋ - የውልን ጉዳይ ስለሚመለከት ማስረጃ ገንዘቡ እንደተከፈለ የሚያስቆጥሩ የህሊና ግምቶች - የፍትሐ ብሔር ህግ ቁጥሮች 1845፣ 2024

የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አመልካች እንዲከፈለው የጠየቀው የጥብቅና አበል በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 2024 (ለ) መሠረት እንደተከፈለ ስለሚቆጠር የሥር ተከሣሾች በአመልካች የተጠየቀውን ገንዘብ ሊከፍሉ አይገባም በማለት ሌሎች ፍ/ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ በመሻሩ የቀረበ አቤቱታ

ውሳኔ: - የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ ጸንቷል።

1. የሕሊና ግምት ድንጋጌዎች ከይርጋ ደንብ ድንጋጌዎች የተለዩ ናቸው።
2. በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2024 በተደነገገው የሕግ ግምት ተጠቃሚ ያልሆነ ወገን (ተከሣሽ) ክፍያው በከፊል መክፈሉ ግምቱን በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2025 (1) መሠረት ቀሪ አያደርግም።

ሐምሌ 29 ቀን 1997 ዓ.ም
የመዝገብ ቁ.15493

ዳኞች መንበረፀሐይ ታደሰ
ፍሥሐ ወርቅነህ
አብዱልቃድር መሐመድ
ስንዱ ዓለሙ
ሂሩት መለሰ

አመልካች ----- አቶ ጳውሎስ ሩምቾ
መልስ ሰጪ -- ወ/ሮ ጫልቱ መርዳሳ

ፍርድ

በዚህ መዝገብ የሰበር አቤቱታ የቀረበው የኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አመልካች እንዲከፈለው የጠየቀው የጥብቅና አበል በፍትሀብሔር ሕግ ቁጥር 2024(ለ) መሠረት እንደተከፈለ ስለሚቆጠር የሥር ተከሣሾች በአመልካች የተጠየቀውን ገንዘብ ሊከፍሉ አይገባም በማለት ሌሎች ፍ/ቤት የሰጡትን ውሣኔ በመሻሩ ነው፡፡

አመልካች ባቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻነት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ በመወሰኑ መልስ ሰጪም በጉዳዩ ላይ ያላትን የጽሁፍ መልስ አቅርባለች፡፡

አመልካች የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት መሠረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽሟል የሚለው (1) ከጥብቅና አበሉ ውስጥ የመጨረሻ ክፍያ የተፈፀመው ሰኔ 1990 ዓ.ም በመሆኑ ክስ እስከቀረበበት ታህሣሥ 18 ቀን 1992 ዓ.ም በፍትሐብሔር ሕግ ቁ.2024 (ለ) የሚጠቀሰው የሁለት ዓመት የጊዜ ገደብ አላለፈም (2) መልስ ሰጪዎች ከፊል ዕዳውን በመፈፀማቸው ዕዳውን እንዳመኑ ስለሚቆጠር በ2024 የተቀመጠው የህግ ግምት በ2025(1) መሠረት ቀሪ ሆኖአል፡፡(3) የጥብቅና ውሉ በጽሁፍ የተደረገ በመሆኑ የይርጋ ጊዜው መታሰብ ያለበት በ10 ዓመት እንጂ በ2024 መሠረት በሁለት ዓመት አይደለም የሚሉትንና ሌሎችንም ተመሳሳይ ክርክሮች በማቅረብ ነው፡፡መልስ ሰጪዋ ጥቅምት 2 ቀን 1997 የተጻፈ ዝርዝር መልስ በማቅረብ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ እንዲፀናላት ጠይቃለች፡፡

አመልካች በመልስ ሰጪ ላይ ጥር 1 ቀን 1992 ዓ.ም ክስ የመሰረተው ጥቅምት 7 ቀን 1988 ዓ.ም በአመልካችና በመልስ ሰጪ መካከል የተመሰረተውን የጥብቅና አገልግሎት ውል መሠረት በማድረግ ነው:: የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ተዋዋዮቹ በውላቸው ላይ ለጥብቅና ውል ምክንያት የሆነው ቤት ለመልስ ሰጪ በገባ በሁለት ወር የጥብቅና ክፍያ መጠናቀቅ እንዳለበት ስለሚገልጽና ቤቱ ሕዳር 1988 መልስ ሰጪ እጅ የገባ በመሆኑ ክስ የቀረበበት የገንዘብ መጠን ክስ በቀረበበት ጊዜ ከሁለት ዓመት በላይ ስለሆነው በ2024 መሠረት እንደተከፈለ ይቆጠራል ብሏል::

ለዚህ ለሰበር ለቀረበው ጉዳይ ምክንያት የሆነው ዕዳ መከፈል ከነበረበት ሁለት ዓመት በላይ እንደሆነው በስር ፍርድ ቤት ተረጋግጦአል:: ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024 ሲሆን በዚህ ድንጋጌ መሠረት በሁለት ዓመት ውስጥ ያልተከፈለ ዕዳ እንደተከፈለ እንደሚቆጠር በዚህ ሰበር ችሎት በመ.ቁ.17068 ትርጉም ተሰጥቶበታል:: የጥብቅና አበል ክፍያን የሚመለከተው የፍ/ብ/ሕ/ቁ.2024(ለ) ም አንዱ የድንጋጌው አካል በመሆኑ በተጠቀሰው ትርጓሜ ውስጥ የሚካተት ነው:: የጥብቅና ክፍያው በሁለት ዓመት ውስጥ ያልተጠየቀ በመሆኑም ለድንጋጌው በተሰጠው ትርጓሜ መሠረት እንደተከፈለ የሚቆጠር ነው:: ስለዚህ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በዚህ ረገድ የፈፀመው የህግ ስህተት የለም:: አመልካች የሕግ ግምትና የይርጋ ህግን በማመሳሰል ጉዳዩ በፍ.ብ.ሕ.ቁ.1845 እንዲታይለት ቢጠይቅም የተያዘው ጉዳይ የክፍያ ግምት እንጂ የይርጋ ጉዳይ ባለመሆኑ ቅሬታው ተቀባይነት የለውም::የክፍያ ግምት ውሉ በጽሁፍ የተደረገ ሲሆን ተፈጻሚ አይሆንም የሚል ህግ ባለመኖሩ አመልካች ውላችን በጽሁፍ ስለሰፈረ በ2024(ለ) ተፈጻሚነት ሊሆንብኝ አይገባም ያለው ተቀባይነት የለውም:: መልስ ሰጪ በከፊል የጥብቅና አበል መክፈላቸውም ቢሆን አሁን ክስ የቀረበበትን ቀሪውን የጥብቅና አበል ማመናቸውን አያመለክትም:: በመሆኑም የሕጉን ግምት ተፈጻሚነት በ2025(1) መሠረት ቀሪ ለማድረግ በቂ ምክንያት አይደለም:: በመሆኑም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ክስ የቀረበበት ብር 71,000(ሰባ አንድ ሺህ) ሁለት ዓመት ካለፈው በኋላ የተጠየቀ ስለሆነ በፍ.ብ.ሕ.ቁ.2024(ለ) መሠረት እንደተከፈለ ይቆጠራል በማለት የሥር ፍ/ቤቶችን ውሣኔ መሻሩ ሕጉን በትክክል ተፈጻሚ ማድረጉን እንጂ የህግ ስህተት መፈፀሙን አያመለክትም::

<u>ውሣኔ</u>

(1) የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁ.00253 በ20/7/96 የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል::
(2) ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ::